# የአዲስ አበባ ዉሃና ፍሳሽ ባለስልጣን

# የፍሳሽ ማጣሪያ ጣቢያ አስተዳደር እና መልሶ መጠቀም መመሪያ

## ቁጥር 15/2012

<u>መግቢያ</u>

በአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስስልጣን የተማከለ እና ያልተማከለ የፍሳሽ ማጣሪያ ጣቢያ አስተዳደር ውጤታማ እና አካባቢን በማይበክል ሁኔታ የተጣራ ፍሳሽ ዝቃጭ እና ጋዝ ለማስወገድ ወጥ የሆነ አሰራር በማስፈን እና መልሶ መጠቀም በማስፈለጉ፤

የባለስልጣን መ/ቤቱ የደንበኞችን ተግባር እና ሃላፊነት በግልፅ ለይቶ ማስቀመጥ ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፤

በባለስልጣን መ/ቤቱ የፍሳሽ ማጣሪያ ጣቢያ አስተዳደር እና መልሶ መጠቀም ሥራዎችን በተመለከተ ቀልጣፋ፣ ውጤታማ ፤ ተጠያቂነት እና ግልጽ የሆነ አሰራር ለማስፈንና ወጥ የሆነ የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት እንዳለበት ስለታመነ፤

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 35/2004 አንቀጽ 53 ንዑስ አንቀጽ 2 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### አንቀጽ/1/

### አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የአዲስ አበባ ውሃና ፍሰሽ ባለስልጣን የፍሳሽ ማጣሪያ ጣቢያ አስተዳዳር እና መልሶ መጠቀም አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 15/2012" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### አንቀጽ 2

### ትርጓሜ

**የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጓሜ የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም የሚከተሉት ቃላትና ሀረጎች ከዚህ በታች የተሰጣቸውን ትርጓሜ ይኖራቸዋል፡**

1. **"ባለስልጣን"** ማለት፡- የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን ማለት ነው፤
2. **"ዋና ሥራ አስኪያጅ "** ማለት፡- የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን ዋና ሥራ አስኪያጅ ማለት ነው፤
3. **"ም/ዋና ሥራ አስኪያጅ"** ማለት፡- የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን የዘርፍ ም/ዋና ሥራ አስኪያጅ እና የፕሮጀክት ሥራ አስኪያጅ ማለት ነው፤
4. **"ሥራ አስኪያጅ "** ማለት፡- የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን የቅ/ጽ/ቤቶች ሥራ አስኪያጅ ማለት ነው፤
5. **"ዘርፍ"** ማለት ፡- የፍሳሽ ቆሻሻ ማንሳትና ማስፋፋት አገልግሎት ም/ዋ/ሥራ አስኪያጅ ማለት ነው፤
6. **"ንዑስ የሥራ ሂደት"** ማለት፡- በዋናው መ/ቤትና በቅርንጫፍ ጽ/ቤት የሚገኙ የፍሰሽ ዘርፍ ንዑስ የሥራ ሂደት ማለት ው፤
7. **"ሠራተኛ"** ማለት፡- በአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን ለተወሰነ ጊዜና ላልተወሰነ ጊዜ የተቀጠሩ ሠራተኞች ማለት ነው፤
8. **"ፍሳሽ"** ማለት፡-የተጣራ ውሃ ለመኖሪያ ቤት፤ለንግድ፤ለኢንደስትሪ፤ለማዘጋጃ ቤት ወይም ለማኅበራዊ አገልግሎት ከዋለ በኃላ በማንኛዉም መጠን/ደረጃ የተበከለ ውሃ ሲሆን ይኽም ዕጣቢ፤የሽንት ቤት ቆሻሻ እና የእነኚሁኑ ዝቃጭ ይጨምራል፤
9. **"የጤና ጽ/ቤት"** ማለት፡- የጤና ስራዎችን በከተማው እንዲመራ በሕግ ስልጣን የተሰጠው የመንግሥት ተቋም ነው፣

10. **"ፍሳሽ ቆሻሻ "** ማለት፡- ከሕዝብ መፀዳጃና ንፅህና መጠበቂያ ቤቶች የሚመነጭ ቆሻሻ ውሃ ወይም ሌላ ፈሳሽ ቆሻሻ ነው፣

11. **"ደረቅ ቆሻሻ "** ማለት፡- ከሕዝብ መፀዳጃና ንፅህና መጠበቂየ ቤቶች አካባቢ የሚገኝ ጥቅም የማይሰጥ ወይም የማያስፈልግ ተብሎ የሚጣል ጠጣርና ከፊል ጠጣር ቆሻሻ ነው፣ አሁን ጥቅም ላይ የማይውል ማለት ነው፣

12. **"ጎርፍ ማስወገጃ መስመር"** ማለት፡- በመንገድ ግራና ቀኝ ለጐርፍ መውረጃነት የሚገነባ ዝግ ወይም ክፍት ቦይ ነው፣

13. **"የተማካለ ፍሳሽ ማጣያ ጣቢያ"** ማለት፡- በከተማው የፍሳሽ መስመር ኔት ወርክ /መረብ / አማካኝነት ተሰብስቦ የሚወገድ ፍሳሽን ለማጥራት የተገነባ የፍሳሽ ማጣሪያ ጣብያ ማለት ነው፡፡

14. **"ያልተማከለ ፍሳሽ ማጣሪያ ጣቢያ "** ማለት፡- በከተማው ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች የፍሳሽ መስመር ኔት ወርክ /መረብ / ባላዳረሰባቸው አካባቢዎች ፍሳሽ በከፊል ወይም በሙሉ ለማጥራት የተገነባ የፍሳሽ ማጣሪያ ጣቢያ ማለት ነው፡፡

15. "ABR (Anaerobic Baffle Reactor)" ማለት፡- በመሬት ስበት በሴኘቲክ ታንክ አማካኝነት ፍሳሽ በከፊል የማጥራት ዘዴ ማለት ነው፡፡

16. "MBR (Membrane Bio Reactor)" ማለት፡- በዘመናዊ ኤሌክትሮ መካኒካል ሂደት ፍሳሽ የማጥራት ዘዴ ማለት ነው፡፡

17. **"ስላጅ / ዝቃጭ/ "** ማለት፡- ከተሰበሰበ የፍሳሽ ቆሻሻ የሚዘቅጠው ወይም የሚደርቀው ተረፈ ምርት ማለት ነው፡፡

18. **"መልሶ መጠቀም"** ማለት፡- በማጣሪያ ጣቢያ ተጣርቶ የሚለቀቀውን ፍሳሽ ፣ ጋዝ ወይም ሰላጅ /ዝቃጭ/ ለተለያየ አገልግሎት እንዲውል ማድረግ ማለት ነው፡፡

19. **"የግል የፍሳሽ አንሺ"** ማለት፡- የፍሳሽ ማንሻ ተሽከርካሪ በግል ባለሀብት ተግዝቶ ፍሳሽን ለማስወገድ የተሰማራ ማለት ነው፡፡

20. MBBR / movable Bed Bioreactor/ ማለት በዘመናዊ ኤሌክትሮ መካኒካል ሂደት ፍሳሽ ማጣራት ዘዴ ማለት ነው፡፡

21. CAS/ Conventional Activated Sludge/ ማለት በዘመናዊ ኤሌክትሮ መካኒካል ሂደት ፍሳሽ ማጣራት ዘዴ ማለት ነው፡፡

22. EAAS/ Extended Aeration Activated sludge/ ማለት በዘመናዊ ኤሌክትሮ መካኒካል ሂደት ፍሳሽ ማጣራት ዘዴ ማለት ነው፡፡

23. UASB / Upflow Anaerobic sludge blanket/ + TF / Trickling Filter/ ማለት በዘመናዊ ኤሌክትሮ መካኒካል ሂደት ፍሳሽ ማጣራት ዘዴ ማለት ነው፡፡

24. **“የማጣሪያ ጣቢያ ኦፕሬተር”** ማለት፡- ፍሳሽ በማጣሪያ ጣቢያ ሲወገድ ደረጃውን በጠበቀ መንገድ እንዲወገድ የማጣራት ሂደት የኦፕሬሽን ስራዎችን የሚከታተል ባለሙያ ማለት ነው፡፡

25. **“የፍሳሽ ተሽከርካሪ ኦፕሬተር”** ማለት፡- ፍሳሽን በተሽከርካሪ አገልግሎት ለማንሳት የሚያሽከረክር ተሽከርካሪውን የሚያንቀሳቅስ ባለሙያ ማለት ነው፤

26. **"የቤቶች ልማት ፕሮጀክት ፅ/ቤት "**ማለት፡- በከተማው የጋራ መኖሪያ ቤቶችን በመገንባት ለነዋሪዎቹ በማስተላለፍ ተጠቃሚ የሚያደርግ መንግስታዊ አካል ነው፤

27. **"ሪል እስቴት "ማለት፡-** በከተማው ክልል ውስጥ መሬት በሊዝ ገዝቶ ቤቶች ገንብቶ የሚሸጥና ለገዥዎች የሚያስተላልፍ ወይም እንደአስፈላጊነቱ የሚያከራይ የግል ድርጅት ነው፤

28. **"የቅድመ ማጣሪያ ደረጃ "ማለት፡-** ከፍሳሽ ቆሻሻ ጋር የሚገቡ ጠጣርና ተንሳፋፊ ቁሶች ለይቶ ማስወገድ ቅደመ ማጣሪያ ደረጃ ይባላል፤

29. **"ማድረቂያ መደብ" ማለት፡-** ፍሳሽ በተሽከርካሪ እና በመስመር ተጣርቶ በማጣሪያ ጣቢያ የሚወገደውን ዝቃጭ የሚደፋበት ማድረቂያ መደብ ነው፤

30. **"የፍሳሽ ማጣሪያ ክለርክ " ማለት፡-** በማጣሪያ ጣቢያ ፍሳሽ በተሽከርካሪ የሚያመጣውን መጠን ፣ ይዘት እና አይነት መረጃ በመያዝ የሚከታተል እና እንዲሁም የሚቆጣጠር ሰራተኛ ማለት ነው፤

31. **"የፍሳሽ ይዘት ምርመራ ባለሙያ" ማለት፡-** ወደ ፍሳሽ ማጣሪያ ጣቢያ የሚገባውን ፍሳሽ በየደረጃው ባሉ የማጣራት ሂደቶች አልፎ ተጣርቶ ሲወጣ የጥራት ደረጃውን በቤተ ሙከራ የሚፈትሹ ባለሙያዎች ማለት ነው፤

32. **"የማጣሪያ ጣቢያ ኬዝ ማናጀር" ማለት፡-** የማጣሪያ ጣቢያው ኃላፊ ነው፡፡

33. "የፍሳሽ ቆሻሻ ማብላያ ኩሬ" ማለት፡- ተፈጥሯዊ በሆነ ሂደት በባክቴሪያና አልጌ አማካኝነት የፍሳሽ ቆሻሻ ማከሚያ ማጣሪያ ጉድጓድ ማለት ነው፤

34. **"ተንሳፋፊ ደረቅ ስላጅ አስወጋጅ" ማለት፡-** በቅድመ ማጣሪያ ደረጃ ተንሳፋፊ ባዕድ ነገሮች ፣ የሚዘቅጡ ነገሮችና ደረቅ ስላጅ የሚያስወግድ ሁለገብ የጉልበት ሰራተኛ ማለት ነው፤

35. **"የአካባቢ የደን ልማት እና የአየር ንብረት ለውጥ ሚኒስቴር"** ማለት፡- ከተለያዩ ተቋማት ወደ አካባቢ የሚለቀቁ የብክለት ልቀት የሚከታተል መንግስታዊ ተቋም ማለት ነው፡፡

36. **"ማዘጋጃ ቤትዊ የፍሳሽ ቆሻሻ" ማለት፡-** ከመኖሪያ ቤት ፣ ከንግድ ተቋማት፣ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት የሚመነጭ ፍሳሽ ቆሻሻ ማለት ነው፤

37. **"የጋራ መኖሪያ ቤት" ማለት፡-** በከተማው በቤቶች ልማት ፕሮጀክት ፅ/ቤት በኩል የተገነቡ ወይም የሚገነቡ እና እድለኛ ለሆኑ ነዋሪዎች በዕጣ ወይም በማናቸውም ሁኔታ የተላለፉ ወይም የሚተላለፉ ኮንዶሚኒየም ቤት የሚባለው ነው፡፡

38. **"የፍሳሽ ማጣሪያ ጣቢያ" ማለት፡-** የፍሳሽ ቆሻሻን አጣርቶ ደረጃውን የጠበቀ ፍሳሽ ጋዝና ዝቃጭ ለማስወገድ ወይም መልሶ ለመጠቀም የሚሰራበት ስፍራ ማለት ነው፤

39. **"ቅርንጫፍ ፅ/ቤት" ማለት፡-** በባለስልጣን መ/ቤቱ ስር የሚገኝና የባለስልጣኑ አካል የሆነ ፅ/ቤት ማለት ነው፤

40. **"የፍሳሽ ማጣሪያ ጣቢያ ሱፐርቫይዘር" ማለት፡-** አጠቃላይ በፍሳሽ ማጣሪያ ጣቢያ የሚሰሩ የኦፕሬሽን ሥራዎች የሚቆጣጠር ባለሙያ ማለት ነው፤

41. **አዲስ አበባ አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን፡-** ማለጽ በከተማ ባሉ የተለያ ተቋማት ወደ አካባቢ የሚለቀቁ የብክለት ልቀት የሚከታተል መንግስታዊ ተቋም ማለት

## <u>አንቀጽ 3</u>

## <u>የመመሪያው ተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ በአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስስልጣን በፍሳሽ ማጣሪያ ጣቢያዎች፣ በግል የፍሳሽ አንሺዎች እና የመልሶ መጠቀም አልሚዎች ተዛማጅ የሥራ ክፍሎች ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>የፍሳሽ ማጣሪያ ጣቢያ አስተዳደርና መልሶ መጠቀም</u>

## <u>አንቀጽ 4</u>

## <u>የፍሳሽ ማጣሪያ ጣቢያ አስተዳዳር</u>

1. ባለስልጣኑ የማጣሪያ ጣቢያዎችን ይገነባል ያስተዳድራል ፡፡
2. በአዲስ አበባ ቤቶች ልማት ፕሮጀክት ፅ/ቤት፣ በሪል እስቴት የሚገነቡ የፍሳሽ ማጣሪያዎችን ግንባታ ጥራትን በማረጋገጥ ይረከባል፣ ያስተዳድራል፣
3. የማጣሪያ ጣቢያ ቅጥር ግቢ እንዲከበር ያደርጋል፤
4. የፍሳሽ ማጣራት ሂደቱን የሚያውኩ ጉዳዮች እንዳይፈጠሩ በማጣሪያ ጣቢያው ኃላፊ አማካኝነት ተገቢ ስራዎችን የማከናወን ግዴታ አለበት፤

5. የፍሳሽ ማጣሪያ ጣቢያ ደረጃውን በጠበቀ እና ሽታን መከላከል በሚችሉ ተክሎች /እፅዋት/ በራስ ኃይል ወይም በሶስተኛ ወገን እንዲሸፈን የማልማት ግዴታ አለበት፡፡

6. ማጣሪያ ጣቢያው ውስጥ ያሉ የማጣሪያ ሂደቱን የሚያከናውኑ ፈፃሚዎች ደህንነታቸው የተጠበቀ የሚያደርግ የሥራ አካባቢ መፍጠር አለበት፣

7. በማጣሪያ ጣቢያ ተጣርቶ የሚወጣው ፍሳሽ አካባቢን በማይበክል እና የአዲስ አበባ አካባቢ ባለስልጣን የሚያወጣውን የደረጃ መስፈርት የሚያሟላ መሆን አለበት፡፡

8. በማጣሪያ ጣቢያው የሚገኙ ማናቸውም ተሽከርከሪ ፣ የኤሌክትሮ መካኒካል መሳሪያዎች እና የፍሳሽ ጥራት ደረጃ የሚያረጋግጡ መሳሪያዎች ደህንነት በሚገባ ይከታተላል ይንከባከባል፣

9. ባለስለልጣን መ/ቤቱ ለማጣሪያ ጣቢያ ግንባታ አስፈላጊውን ጥበቃ ፣ ጥገና እና እድሳት ማድረግ አለበት፤

## <u>አንቀጽ 5</u>

## <u>የተማከለ ፍሳሽ ማጣሪያ ጣቢያ አጠቃቀም ተግባርና ኃላፊነት</u>

### <u>5.1. የተማከለ ፍሳሽ ማጣሪያ ጣቢያ አጠቃቀም</u>

1. ከተፈቀደለት የፍሳሽ ማንሻ ተሽከርካሪ ውጭ እንዲሁም ማጣሪያ ጣቢያው ውስጥሊደፉ የሚችሉ የፍሳሽ አይነቶች ውጭ ወደ ማጣሪያ ጣቢያው ገብቶ ፍሳሽ መድፋት ፈፅሞ የተከለከለ ነው፤
2. ከማጣሪያ ጣቢያው የሚወጣው ፍሳሽ የአካባቢ ደን ልማትና አየር ንብረት ለውጥ ሚኒስቴር በሚያወጣው መስፈርት መሰረት የጥራት ደረጃውን አሟልቶ መለቀቅ አለበት፤
3. የፍሳሽ ማጣሪያ ጣቢያው ፍሳሽን ለደፋው ተሽከርካሪ ስለመደፋቱ ደረሰኝ ሊሰጠው ይገባል፤

#### 5.1.1. <u>የተማከለ የፍሳሽ ማጣሪያ ጣቢያ ተግባርና ኃላፊነት</u>

1. በመስመር ወደ ፍሳሽ ማጣሪያ ጣቢያ የሚገባን ፍሳሽ ዓይነት በፍሳሽ ማጣሪያ ኦፕሬተር /ሱፐርቫይዘር/ አማካኝነት የመቆጣጠር ሃላፊነት አለበት፡፡

2. የፍሳሽ ማጣሪያ ክለርክ እና ተንሳፋፊ ደረቅ እስላጅ አስወጋጅ ከተፈቀደለት የፍሳሽ ማንሻ ተሽከርካሪ ውጭ ወደ ማጣሪያ ጣቢያው ገብቶ ፍሳሽ እንዳይደፋ ይከታተላል ፣ ይቆጣጠራል ፣ ተደፍቶ ከተገኘ ጉዳዩን ወዲያውኑ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ያቀርባል፡፡
3. ተንሳፋፊ ደረቅ እስላጅ አስወጋጅ የፍሳሽ ማጣሪያ ኩሬ በየጊዜው ከተንሳፋፊ፣ ከአረምና ከመሳሰሉት የፀዳ እንዲሆን ያደረጋል፡፡
4. የፍሳሽ ጥራት ቁጥጥር ባለሙያ ተጣርቶ የሚወጣውን የፍሳሽ የጥራት ደረጃ በየወቅቱ መርምሮ መረጃ በመያዝ ውጤት ሪፖርት ያደርጋል፡፡
5. የሚነሳው ሰላጅ ከመደቡ ለማንሳት የእስላጅን የእርጥበት ሁኔታ በፍሳሽ ፅራጽ ባለሙያ መረጋገጥ አለበት፡፡
6. የሚነሳው እስላጅ በማጣሪያ ጣቢያው ሱፐርቫይዘር እና ኦፕሬተር አማካኝነት በተቀመጠው የጊዜ እስታንዳርድ ጠብቆ የማንሳትና በተገቢው ቦታ እንዲከማች ያደርጋል፡፡
7. በፍሳሽ ማጣሪያ ጣቢያ የደፉ ተሽከርከሪዎችን በየቅርንጫፍ በመለየት ለዋና መ/ቤት ፍሳሽ ማንሳት የሥራ ሂደቱ በዝርዝር ሪፖርት ማድረግ አለበት፡፡
8. . የፍሳሽ ማጣሪያ ጣቢያው ፍሳሽ ለሚደፉ ተሽከርካሪዎች ማጠቢያ ውሃ ያዘጋጅል፡፡፡
9. ከቅርንጫፍ ፍሳሽን ከደንበኛዉ እንዲነሳ ከተዘረዘሩት የሥራ ትዕዛዝ ውጪ አለመሆኑን ያረጋግጣል፡፡ ልዩነት ካለ እንዳይደፉ ያደረጋል፡፡ የሰራውን ኦኘሬተርና ረዳት ኦፐሬተር እንዲሁም የተሽከርካሪውን ሰሌዳ ቁጥር ቀን እና ሰዓቱን በመመዝገብ ለኬዝ ቲሙ እና ለዋናው መ/ቤት ፍሳሽ ማንሳት ንኡስ የስራ ሂደት ሪፖርት ማድረግ አለበት፡፡
10. የግል የፍሳሽ አንሺዎች አገልግሎቱን ለመስጠትና በጣቢያው እንዲደፉ ወይም ከባለስልጣኑ ጋር ውል በመግባት እንዲያስወገዱ የተፈቀደ መሆኑን በጣቢያው ክለርክ አማካኝነት መረጋገጥ አለበት፡፡
11. በየዕለቱ የግል ፍሳሽ ተሽከርካሪ የሚወገደው የፍሳሽ ምልልስ መጠኑን የተደራጀ ሪፖርት መያዝና ለሚመለከተው ሪፖርት ማድረግ አለበት፡፡
12. ተንሳፋፊና ደረቅ ስላጅ አስወጋጅ የሰፍሳሽ ማጣሪያ ኩሬ በየጊዜው ከተንሳፋፊ ነገሮች ከአረምና ከመሳሰሉት ነገሮቸ የፀዳ እንዲሆን ያደርጋል፡፡
13. በኤሌክተሮ መካኒካል የሚንቀሳቀሱ ማጣሪያ ጣቢያዎች እንደ UASB + TF የማጣሪያ ጣቢያ ሂደቱ ተገቢውን ሁኔታ ማካሄዱን በተመደቡ ባለሙያዎች አማካኝነት ይከታተላል፡፡
14. የማጣሪያ ጣቢያውን የመጠባበቂያ ጀኔሬተር እና ኤሌክተሮ መካኒካል እቃዎችን ደህንነት በፍሳሽ ማጣሪያ ጣቢያው ሱፐርቫይዘር ወይም ኦፕሬተር አማካኝነት ይከታተላል ፣ይቆጣጠራል፡፡
15. የመጠባበቂ ጀኔሬተር ነዳጅን በፍሳሽ ማጣሪያ ጣቢያው ኦፕሬተር አማካኝነት ወጭ በማድረግ በአግባቡ ይጠቀማል ፣አጠቃቀሙን በተመለከተ በየሳምንቱ ሪፖርት ያቀርባል፡፡

## 5.2. ያልተማከለ የፍሳሽ ማጣሪያ ጣቢያ አጠቃቀም

1. የሪል እስቴት አልሚ ባለሀብቶች ያልተማከለ የፍሳሽ ማጣሪያ ጣቢያ በራሳቸው ወጭ ሊያስገነቡ ይችላሉ፡፡ ሆኖም ዲዛይንና የግንባታ ቁጥጥርን ባለስልጣኑ ያረጋግጣል ያስተዳድራል፡፡
2. ካልተማከለ የፍሳሽ ማጣሪያ ጣቢያ የሚነሳ ሰላጅ/ ዝቃጭ/ ፍሳሽ በማጣሪያ ጣቢያው ሰኪፐ ኦፕሬተር አማካኝነት ጊዜውን ጠብቆ ወደ ማድረቂያ ጣቢያ ወይም ቋሚ ማከማቻ ጣቢያ መዘዋወር አለበት፡፡
3. የABR ማጣሪያ ጣቢያ ሂደት በማዕከል ወይም በቅርንጫፉ ለዚሁ ስራ ተብለው በግልፅ በሚመደቡ ባለሙያዎች አማካኝነት በየወቅቱ ክትትል መደረግ አለበት፡፡
4. ከማጣሪያ ሂደቱ የሚወጣውን ፍሳሽ /ውሃ/ ለተለያዩ አገልግሎቶች ለግንባታ፣ ለአትክልት፣ ለመንገድ ሥራ ወዘተ. መልሰው ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ አለበት፡፡
5. ከማጣሪያ ሂደት የሚወጣውን ዝቃጭ መልሶ ለመጠቀም እንዲቻል ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ጥቅም ላይ ያውላል፡፡
6. በኤሌክትሮ ሜካኒካል የሚንቀሳቀሱ ማጣሪያ ጣቢያዎች (እነደ MBBR,MBR,CAS,EAAS) ላይ ቋሚ ኦኘሬተሮች፤ ፈፃሚዎች ይመድባል በሚቀመጠው የስራ ሰዓት ድልድል መሰረት በ24 ሰዓት ውስጥ በተለያየ የስራ ፈረቃ /ሽፍት/ እንዲሰራ ይደረጋል፡፡

### 5.2.1.ያልተማከለ የፍሳሽ ማጣሪያ ጣቢያ ተግባርና ኃላፊነት

1. ያልተማከለ የፍሳሽ ማጣሪያ ጣቢያ የፍሳሽ መረብ በለሌበት አከባቢ ባለስልጣን መ/ቤት ያልተማከለ ፍሳሽ ማጣሪያ ጣቢያ በራሱ ወጭ ወይም በደንበኞች ወጭ ሊያከናውን ይችላል፡፡
2. መንግስት የሚያስገነባቸው የጋራ መኖሪያ ቤቶች ያልተማከለ የፍሳሽ ማጣሪያ ጣቢያ የግንባታ ወጪን አሰሪው አካል ይሸፍናል፡፡ የግንባታ ወጭ ሽፋኑ እንደተሰጠው እንደዲዛይኑ ሲጠናቀቅ ባለስልጣኑ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ይረከባል፡፡ ግንባታውን ባለስልጣኑ በራሱ ወይም በሶስተኛ ወገን ሊያሰራ ይችላል፡፡
3. ከABR ማጣሪያ ጣቢያ የሚወጣው የፍሳሽ ጥራት ይቆጣጣራል፤ ደረጃውን የጠበቀ ካልሆነም ማስተካከያ እንዲወስድ በማጣሪያ ጣቢያው ሱፐርቫይዘር/ኦፕሬተር አማካኝነት ይደርጋል፡፡

4. የማጣሪያ ጣቢያውን የመጠባበቂያ ጀነሬተር እና ኤሌክትሮ ሜካኒካል እቃዎችን ደህንነት በፍሳሽ ማጣሪያ ጣቢያው ሱፐርቫይዘር ወይም ኦፕሬተር አማካኝነት ይከታተላል ይቆጣጠራል፡፡
5. የመጠባቢቂያ ጀነሬተር ነዳጅን በፍሳሽ ማጣሪያ ጣቢያው ኦፕሬተር አማካኝነት ወጪ በማድረግ በአግባቡ ይጠቀማል አጠቃቀሙን በየሳምንቱ ሪፖርት ያቀርባል፡፡
6. በኤሌክተሮ መካኒካል የሚንቀሳቀሱ ማጣሪያ ጣቢያዎች / MBBR,MBR,CAS,EAAS/ የማጣሪያ ሂደቱ ተገቢው ሁኔታ መካሄዱን በተመደቡ ባለሙያዎች አማካኝነት ይከታተላል፡፡
7. የፍሳሽ ማጣሪያ ጣቢያ ኦፕሬተር የማጣሪያ ጣቢያውን አጠቃላይ የማጣራት ሂደት በየእለቱ በተዘጋጀው / Log sheet/ እየሞላ ለሚመለከተው ክፍል ሪፖርት ያደርጋል፡፡

## አንቀጽ 6

## የግል ፍሳሽ በተሽከርካሪ አንሺዎችን በተመለከተ

1. የግል የፍሳሽ አንሺ ተሽከርካሪዎች በተቋሙ የፍሳሽ ማጣሪያ ጣቢያ ፍሳሽ ማስወገድ ይችላል፣
2. የባለስልጣኑን ሕግ ደንቦችና የቴክኒክ መመሪያዎችም በተለይ ስለፍሳሽ አወጋገድ የወጡ የጥራት መመዘኛዎችን ማክበር አለበት፤
3. በባለልስጣኑ የፍሳሽ ማጣሪያ ጣቢያ ለሚደፋው ፍሳሽ በተቀመጠው ታሪፍ መሠረት ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ መከፈል አለበት፤
4. የሰበሰውን ፍሳሽ በሚዘጋጀው ማጣሪያ ገንዳ ወይም እንደወቅቱ ሁኔታ ሥራው እመቺ ሆኖ በተገኘበት ቦታ እንዲደፋ ሲታዘዝ በተባለው ቦታ የመድፋት ግዴታ አለበት፡፡
5. ማጣሪያ ጣቢያው በሚያስቀምጠው የስራ ሰዓት ወይም ጊዜ ውስጥ የመድፋት ወይም የመገልገል ግዴታ አለበት፡፡
6. በየዕለቱ የተወገደውን የፍሳሽ መጠን እና ምልልስ ብዛትን ሪፖርት ማቅርብ አለበት፡፡

## አንቀጽ 7

## የፍሳሽ ማድረቅያ መደብ አጠቃቀም

1. በተሽከርካሪ የሚደፋ ፍሳሽ ወደ ማድረቂያ መደብ ከመግባቱ በፊት የቅድሚያ ማጣሪያ መደረግ አለበት፡፡

2. ከማድረቅያ መደብ የሚነሳውን ሰላጅ /ዝቃጭ/ በተቀመጠው የጊዜ እስታንዳርድ ጠብቆ የማንሳትና በተገቢው ቦታ ማከማችት አለበት፡፡
3. ተንሳፋፊና ደረቅ ስላጅ አስወጋጅ ሰራተኞች የማድረቂያ መደቡ በተሽከርካሪ ተሰብስቦ መጥቶ የተደፋውን ፍሳሽ ባዕድ ከሆኑ ተንሳፋፊ፣ ጠጣር፣ ከአረም እና ከመሳሰሉት ያፀዳሉ፡፡
4. የማጣሪያ ጣቢያ ሱፐርቫይዘር / ኦፕሬተር/ በተሽከርካሪ ተሰብስቦ እና በመስመር ከሚገባው ፍሳሽ ተጣርቶ የሚወጣውን ዝቃጭ ፍሳሽ ማድረቂያ መደብ ላይ ሲደርቅ በአማካይ እስታንዳርድ 20 ሴ.ሜ ውፍረት ወይንም ጥልቀት እንዲሆን ተደርጎ እንዲደፋ ይከታተላል ፤ ስለዚህ በዚህ ሁኔታ ተደፍቶ የተሞላ ማድረቂያ መደብ በፀሀይ ሙቀት ተሰጥቶ እንዲደርቅ እስከ 3 ወር ያስፈልገዋል፡፡

**<u>አንቀጽ 8</u>**

**<u>ፍሳሽን መልሶ ስለ መጠቀም</u>**

1. በጥናት የተደገፈ ከፍሳሽ ማጣሪያ ጣቢያው በማጣራት ሂደት የሚወጣው ዝቃጭ፣ ፍሳሽ እና ጋዝን መልሶ መጠቀም ይችላል፣
2. ከፍሳሽ ማጣሪያ ጣቢያው የሚወጣ የተጠራ ፍሳሽ፣ ሰላጅ እና ጋዝ አካባቢን በማይበክል ሁኔታ ለመልሶ መጠቀም እንዲያስችል መዘጋጀት አለበት፡፡
3. የመልሶ መጠቀም ሥራን ባለስልጣኑ በራሱ ወይም በሶስተኛ ወገን ሊያሰራ ይችላል፣
4. በሶስተኛ ወገን ለሚሰሩ የመልሶ ማልማት ስራዎች ባለስልጣኑ መሬት ፣ ውሃ፣ የሃይል ምንጭ እና ሌሎች አስፈላጊ መሰረታዊ ነገሮችን ያሟላል፣
5. ፍሳሽን መልሶ ጥቅም ላይ ለማዋል፣ የእርሻ እና የተፈጥሮ ሃብት ልማት ስራ ላይ የተሰማሩ ድርጅቶችን ባለስልጣኑ በልዩ ሁኔታ ያበረታታል፡፡
6. ከፍሳሽ ማጣሪያ ጣቢያው የሚወጣን የተጣራ ፍሳሽ፣ ሰላጅ /ዝቃጭ/ እና ጋዝ ባለስልጣኑ በክፍያ ወይም እንደሁኔታው በነፃ ለአልሚው ሊሰጥ ይችላል፡

7. የመልሶ መጠቀም አልሚ ድርጅት ከባለስልጠኑ በሚፈፀመው የውል ስምምነት መሠረት ሥራውን ማከናወን አለበት፡፡

8. በመልሶ መጠቀም ዙሪያ ለሚሰሩ ማናቸውን የምርምር እና የስርፀት ሥራዎች ከከፍተኛ ትምህርት እና ከምርምር ተቋማት ጋር በጋራ ባለስልጣኑ መስራት ይችላል፡፡

9. በጥናት እና በምርምር የተገኙ የመልሶ መጠቀም ሃሳቦችን ተግራዊ ለማድረግ አቅሙን ባገናዘበ ሁኔታ ባለስልጣኑ መንቀሳቀስ አለበት፣

10. የመልሶ መጠቀም ሥራን የሚሰሩ ሰራተኞች ላይ ሊከሰቱ የሚችሉ የጤና ችግሮችን የቅድመ መካላከል ሥራ አልሚው መሰራት አለበት፣

11. ለህብረሰተቡ ፍጆታ ጥቅም ላይ የሚውሉ የእርሻ ውጤቶች ደህንነታቸቸው መጠበቅ አለበት፡፡

12. ተከማችቶ የሚገኘውን እና ወደፊት የሚሰበሰበውን ፍግ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመጠቀም የተፈጥሮ ማዳበሪያ ለሚያመርቱ እና በእርሻ ስራ ላይ ለተሰማሩ አካላት የማስተዋወቅ ሃላፊነት አበለት፡፡

## አንቀጽ 9
## ከፍሳሽ ማጣሪያ ጣቢያ የሚወገደውን ፍሳሽ ለመጠቀም አስፈላጊ ቅደመ ሁኔታዎች

1.የአካባቢውን ስነ - ምህዳር በማያውክ እና ተስማሚ በሆነ መንገድ መጠቀም የሚችል መሆን አለበት፡፡

2.ፍሳሽ ሊያጣሩ የሚችሉ ተፈጥሮአዊ ዕፅዋትን /የሳር ዘሮችን/ በመጠቀም የፍሳሽ ማጣራት ሂደትን በሚገባ ጥራቱን የጠበቀ እንዲሆን የማድረግ አቅም ያለው መሆን አለበት፡፡

3.የተጣራ የፍሳሽ ቆሻሻን መልሶ በመጠቀም የሚገኝ የእርሻ ምርት ተጠቃሚዎች ዘንድ ሲደርስ የጤና እና የአካል ጉዳት ስጋት ሊያስወግድ የሚችል አሰራርን ወይም ዘዴን የሚፈጥር መሆን አለበት፡፡

4.ይህን ስራ የሚሰራው አካል ለተለያዩ የህብረሰብ አገልግሎቶች /መዝናኛ፣ ጉብኝት፣ ሰብሰባ ወዘተ/ በሚመች መልኩ አካባቢዉን ደረጃውን በጠበቀ ውብ ለማድረግ ከተቋሙ ጋር ውል ለመግባት ፈቃደኛ የሆነ፤

5.በመልሶ መጠቀሙ ሥራ ለአካባቢው ነዋሪዎች የሥራ ዕድል መፍጠር የሚችል መሆን አለበት፡፡

6.በውል ተከልሎ የሚሰጠውን ቦታ የመጠበቅ እና የማስተዳደር ግዴታ የሚወሰድ መሆን አለበት፡፡

7.በዘርፉ የሚሰማራ አካል በጽዳትና ውበት ወይም በተፈጥሮ ሃብት አጠባበቅ ሥራ ጋር ተያይዞ ችሎታ እና ልምድ ያለው ወይም ብቁ ሙያተኛ ያቀፈ /የቀጠረ/ መሆን አለበት፡፡

## አንቀፅ 10

## የፍግ (Sludge Cacke) አጠቃቀም

1. በተጥሮአዊም ሆነ በቴክኖሎጂ የተደገፈ የማዳበሪያ ምርት በማምረት ዝግጁ ሲሆን እና ለዚህም የመነሻ ካፒታሉ በግልፅ ተግባሩን ማሳካት የሚችል መሆን አለበት፡፡
2. በዘርፉ የሚሰማራ በእርሻ ሥራ ወይም በተፈጥሮ ሃብት ሥራ ጋር ችሎታ እና ልምድ ያለው መሆን አለበት፡፡
3. የፍግ መልሶ መጠቀም ሥራን በሚሰሩ ሰራተኞች ላይ ሊከስት የሚችል የጤና የአካል ጉዳት ችግሮችን አስቀድሞ የመከላከል እና ጉዳት ድንገት ቢደርስም ሁኔታውን የማስተካከል አሰራርን አልሚው መከተል አለበት፡፡
4. የተጣራ የፍሳሽ ቆሻሻን መልሶ በመጠቀም የሚገኝ የእርሻ ምርት ተጠቃሚዎች ዘንድ ሲደርስ የጤናን ስጋት ሊያስወግድ የሚችል አሰራር የሚፈጥር መሆን አለበት፡፡
5. በመልሶ መጠቀሙ ሥራ ለአካባቢው ነዋሪዎች የሥራ ዕድል መፍጠር የሚችል መሆን አለበት፡፡
6. በውል ተከልሎ የሚሰጠውን ቦታ የመጠበቅ እና የማስተዳደር ግዴታ የሚወሰድ መሆን አለበት፡፡
7. አልሚው ከሚያገኘው ገቢ ለባለስልጣኑ በውል በተቀመጠው መሰረት ክፍያ ለመፈጸም ፈቃደኛ መሆን አለበት፡፡

## አንቀፅ 11

## የ Bio-Gas አጠቃቀም

1. በባዮ ጋዝ ምርት ስራ ላይ ለመሳተፍ የመዕዋለ ንዋይ እና የሙያ ብቃት ያለው መሆን አለበት፡፡
2. ከሀገሪቱ የኤሌክትሪክ እና ጋዝ የአሰራር መመሪያን አክብሮ መሰራት አለበት፡፡
3. ከሚያገኘው ገቢ ለባለስልጣኑ በውል በተቀመጠው መሠረት ክፍያ ለመፈፀም ፍቃደኛ መሆን አለበት፡፡
4. በውል ተከልሎ የሚሰጠውን ቦታ የመጠበቅ እና የማስተዳደር ግዴታ የሚወሰድ መሆን አለበት፡፡
5. በመልሶ መጠቀሙ ሥራ ለአካባቢው ነዋሪዎች የሥራ ዕድል መፍጠር የሚችል መሆን አለበት፡፡

## አንቀጽ 12

## ከአገልግሎት ስለሚገኝ ክፍያ

1. የግል ፍሳሽ አሽከርካሪዎች ባለስልጣኑ በሚያወጣው የአገልግሎት ክፍያ መሰረት ክፍያን የመክፈል ግዴታ አለባቸው፡፡
2. በመልሶ መጠቀም የሚሰማሩ አልሚዎች በሚደረገው ውል የተቀመጠውን የመጠቀሚያ ክፍያ ለመክፈል ፈቃደኛ የሆኑ መሆን አለባቸው፡፡

## ክፍል ሶስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች
## አንቀፅ 13

## ቅጣት

1. ማንኛውም የግል የፍሳሽ አንሺ በሕገወጥ መንገድ ፍሳሽ ካስወገደ ወይም በባለስልጣኑ ስለፍሳሽ አወጋገድ የወጡ ህጎችን ደንቦችና የቴክኒክ መመሪያዎችን ካላከበረ ወይም ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ ካልከፈለ ባለስልጣኑ የግል ፍሳሽ አንሺ ባለንብረቱን የፍሳሽ ማንሻ አገልግሎት እንዳይሰጥ ለተወሰነ ጊዜ ለማቋረጥ ይችላል፡፡

2. በተጨማሪም የድርጊቱ ፈፃሚ አግባብ ባለው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ድንጋጌ መሠረት ያለበት ተጠያቂነት እንደተጠበቀ ሆኖ በሕገወጥ መንገድ ፍሳሽ ማስወገዱ ላስከተለው ወጪ ኪሳራ ኃላፊ ይሆናል፡፡

3. በዚህ መመሪያ ላይ ጥሰት የሚፈፅም ደንበኛ ውል ማቋረጡ እንደተጠበቀ ሆኖ አግባብነት ባላቸው የወንጀልና ፍትሐ ብሄር ህጎች ተጠያቂ ይሆናል፡፡

4. በዚህ መመሪያ ላይ ጥሰት የሚፈፅም ሰራተኛ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 እና በህብረት ስምምነቱ መሠረት የዲሲፕሊን ቅጣት እና አግባብነት ባላቸው የወንጀልና ፍትሐብሄር ሕጎች ተጠያቂ ይሆናል፡፡

5. በዚህ መመሪያ ላይ ጥሰት የሚፈፅም አመራር በስራ መሪዎች መተዳደሪያ ደንብ መሰረት እና አግባብነት ባላቸው የወንጀልና ፍትሐ/ብሄር ህጎች ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 14
## ተፈጻሚነት ስለሚኖራቸው ህጎች

ተፈፃሚነት ያላቸው ህጐች አዋጅ ቁጥር 377/96፣ የሕብረት ስምምነት፣ የሥራ መሪዎች መተዳደሪያ ደንብ እና አግባብነት ያላቸው የፍትሀ ብሄር እና የወንጀል ህጎች ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

## አንቀፅ 15

## የመተባበር ግዴታ

ይህንን መመሪያ ለማስፈጸም በየትኛውም ደረጃ ያሉ የባለስልጣኑ ኃላፊዎች፣ ሰራተኞች ፣የሚመለከታቸው መንግስታዊም ሆነ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ወይም ህግና ደንብ እንዲያስከብሩ ስልጣን የተሰጣቸው አካላት፣ ማንኛውም ሰው እና ደንበኞች የመተባበር ግዴታ አለባቸው፡፡

## አንቀፅ 16

## ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ደንቦች

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረኑ ሌሎች መመሪያዎች ወይም አሰራሮች በዚህ መመሪያ ውስጥ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፡፡

## አንቀፅ 17

## መመሪያው ስለሚሻሻልበት ሁኔታ

ባለስልጣኑ አስፈላጊ ሆኖ ባገኘው በማንኛውም ጊዜ መመሪያውን ሙሉ ለሙሉ ወይም በከፊል ሊያሻሽል ይችላል፡፡

## አንቀጽ 18

## መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በባለሥልጣኑ ዋና ሥራ አስኪያጅ ተፈርሞና የባለሥልጣኑ ማህተም ካረፈበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አቶ አወቀ ኃ/ማሪያም

የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን

ዋና ሥራ አስኪያጅ